# የፅዳት ደህንነት መጠበቂያ ምክሮች ወረቀት

በፅዳት ኢንዱስት ላይ ከስራ ጋር የተያያዙ ጉዳቶችን ለመከላከል ተከታታይ የጤናና ደህንነት ምክሮች



## ንቁ አድማጭ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?

እትም: 8, መጠን: 1

ያልተከፋፈለ ትኩረት ማድረግ።

ከሰራተኞች ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ፣ ያልተከፋፈለ እና ሙሉ ትኩረትዎን ይስጧቸው።

- የስራ ባልደረቦችዎ በሚናገሩበት ጊዜ አያቋርጧቸው።
- ማብራሪያ የሚያስገኙ ጥያቄዎችን ይጠይቁ



የተነገረን ነገር በራስ አገላለጽ መድገም።

ሊፈጠር የሚችል አለመግባባትን ለመቀነስ፣ አንድ የተነገረን መግለጫ በራስ አገላለጽ መድገም።

እያዳመጡ መሆኑን ለማሳየት ጠቅለል አድርጎ አስተያየቶችን  መስጠት

- ለምሳሌ፡ “እና በትክክል ተረድቼህ ከሆነ፣ እይያልክ ያለኸው ...?”
- “እየተረዳሁት ያለሁት ምንድን ነው ...”



የሰውነት ቋንቋ።

እያሳዩ ስላለው የሰውነት ቋንቋዎ ጥንቃቄ ያድርጉ።

- ፈገግ ይበሉ።
- ጥሩ የዓይን ለዓይን ግንኙነት ያድርጉ።
- እጆችዎን በመዘርጋት የሚያቀራርብ አይነት አቋቋም ያሳዩ።
- እያዳመጡ እንደሆነ ለማሳየት ጭንቅላትዎን ይነቅንቁ።



እንደሚከተሉት ያሉ-ግልጽ የሆኑ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፥

a. "ጉዳዩን በምን መንገድ እንድፈታው ትፈልጋለህ?"

b. "ይህ ነገር ሲከሰት የተሰማህ ምንድን ነው"



ሙሉ ትኩረትዎን ለመስጠት ይችሉ ዘንድ፣ ሃሳብዎን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ይቀንሱ።

- ወደ ስልክዎ ወይም ሰዓትዎ አይመልከቱ
- ስራ ነክ ስለሆኑ ጥያቄዎች ወይም ጉዳዮች ለመወያየት ሌላ ጊዜ ይጠቁሙ።



## ጥሩ አድማጭ ስለመሆን ጠቃሚ ምክሮች፥

| **የሚከተሉትን ያድርጉ** | **የሚከተሉትን አያድርጉ** |
| --- | --- |
| ከሚናገሩት በላይ ያድምጡየበለጠ | ውይይቱን ለመቆጣጠር አይሞክሩ |
| መልስ ከመስጠትዎ በፊት ተናጋሪው ተናግሮ እንዲጨርስ እድሉን ይስጡ | ሌሎች ሲናገሩ አያቋርጡ |
| ግልጽ የሆኑ ጥያቄዎችን ይጠይቁ | ተናጋሪው የጀመረውን አረፍተ ነገር ለመጨረስ አይሞክሩ |
| ቀድመው የያዙትን አሉታዊ ሃሳብ ይቀንሱ | ለመደምደም አይቸኩሉ |
| ለሚቀርቡ ሃሳቦች እና ችግር ለሚፈቱ እድሎች ትኩረት ይስጡ | ውንጀላ ወይም ወቀሳ ባዘሉ ቋንቋዎች ምላሽ አይስጡ |
| እያዳመጡ መሆንዎን የሚያሳዩ የቃል እና የቃል ያልሆኑ መልዕክቶችን ይስጡ | ተከራካሪ አይሁኑ |
| ስሜቶች እና የንግግሩን ይዘት ያዳምጡ | ትዕግስት አልባነትን ወይም ብዙ ስራ የማዘዝ ባህሪ አያሳዩ |